# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ሽብርና አምባ-ገነንን ተቋቁሞ ለአዲስ ሥርዓት ግንባታ መጣኝ ትግል፤
## ሕዝባዊ ሰላማዊ ትግል ስንል፤

የኢሕአዴግ መሪዎች የተያያዙት የቅልበሳ ሂደት አንዱ ገፅታው ግንቦትን ያስቻሉትን የፖለቲካ፣ የአስተሳሰብ፣ የተቋማት ግኝቶች እንዳልነበሩ አድርገው በማውደም በአፈናናና በሽብር መጨረሻው ለማይታይ ረጅም ወቅት በኅብረተሰባችን የሽግግር ክፍተት የመፍጠር ሂደት ነው፡፡ እነዚኽ ፀረ-ሕዝብ ኃይሎች በሕዝባችን ተጋድሎ ከጥፋት ሂደታቸው እንዲያፈገፍጉ ከመገደዳቸው በፊት ከእንግዲህ የሕግ የበላይነት፣ የዳኝነት ነፃነት፣ ተጠያቂነት፣ የፕረስ ነፃነት፣ በነፃ የመደራጀት መብት፣ ነፃ ምርጫ፣ ወዘተ.. የሚሉ ከባድ ከባድ እሴቶች ቀርቶ በቅድመ-ግንቦት ወቅት የነበሩት የዴሞክራሲ ፍንጮች እንኳ እውን የሚሆኑበት ምንም ዓይነት ተአምር አይኖርም፡፡ ከዚኽ አንፃር የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ደግሞ ደጋግሞ ያስተጋባው ጥሪ **ሁላችንም ለግንቦት ድሎች ብለን እንነሳ የሚል** ነው፡፡ ይኽ ማለት ግንቦትን ያስቻሉትና ዛሬ ደብዛቸው የጠፋው የዴሞክራሲ መብት ፍንጮች መልሰው እውን እንዲሆኑ መታገል ብቻ አይደለም፡፡ የኢሕአዴግ መሪዎች ዛሬ ባሉበት የኪሣራና በሕዝብ የመተፋት ደረጃ ባልተሟላ ሁኔታ እውን የነበሩ ቢሆኑም እነዚህ መብቶች እርግጥ ሕዝባችን የፈለገውን እንዲመርጥ አስችለውት ነበር፡፡ ነገር ግን ድምፁን ለማስከበር ብቁ እንዳልነበሩ የዚያኑ ያኽል ግልፅ ይመስለናል፡፡ ለዚኽ ነው **"ለግንቦት ድሎች" መታገል** ባልን ቁጥር **"በዚያው ሂደት በነሱው ላይ መገንባት"** እያልን ትግላችን መሥመር የሳተው የዴሞክራሲ ሂደቱ (ዴሞክራታይዜሽን) መልሶ በእግሩ እንዲቆምና ሂደቱ ቀጥሎ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሰፍኖ የዚኽ ሁሉ መቋጠሪያ በሆነው ነፃና ርቱኣዊ ምርጫ እንዲቋጭ ሳያቋርጥ መቀጠል ያለበት ታሪካዊ ተጋድሎ ነው የምንለው፡፡

ለዚኽ ነው ከእንግዲህ ይኽ ፀረ-ሕዝብ ሥርዓት በሕዝብ ኃይል ተገዶ ዴሞክራሲ ከመስፈኑ በፊትና ምርጫም ከተባለ ነፃ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካል (ቦርድ) በሌለበት ሁኔታ ስለ ምርጫ ማውራት በሕዝብ ትግል ማሾፍ የሚሆነው፡፡ ለዚኽም ነው ከእንግዲህ ትግላችን እንደ ቅድመ-ግንቦቱ ወቅት በምርጫ ዙሪያ ሳይሆን ሕዝባዊ የትግል ማዕበል ለመቀስቀስና ለመምራት መሆን ይኖርበታል የምንለው፡፡ ስለሆነም የዴሞክራሲ ፍንጮች በነበሩበት ሁኔታ እንኳን አልጋ-በአልጋ ያልነበረው የዚኽ ሰማዕት ሕዝብ ትግል ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ውስብስብ፣ በጣም ከባድና የበለጠ መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ሂደት ይሆናል የምንለው፡፡ ለዚኽም ሁሉ ነው በዚኽ ታሪካዊ ተጋድሎ "እንኖርበታለን" ብለን በሕዝባችን ፊት ቃል ከገባንና ይኽንን ቃላችንን ከምር ከወሰድን አይቀር ለተቀበልነው ተልዕኮና ላለንበት አዲስ የትግል ምእራፍ በሚመጥን ሁኔታ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረትን አወቃቀር አባል ድርጅቶች ከየድርጅች ነፃነታችን ቀንሰን ለጋራው ትግል በሚያስረክብና የሥራ ቅልጥፍናን የበለጠ በሚያመቻች መልክ ለማሻሻል የመረጥነውና የጥምረት አደረጃጀትንና አወቃቀርን የመረጥነው፡፡

ይኽንን የዴሞክራሲ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) ትግል ከግቡ ለማድረስ ከፈለግን

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73796
Washington DC 20056-3796, U.S.A
ስልክ ቁ./Tel.

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
ስልክ Tel/Fax 31 70 394 6132

የግባችን ትልም (የስትራቴጂያችን) ሁሉ መነሻ ግንቦት የሚሊዮኖች ድል እንደነበረ ሁሉ እነዚኽን ድሎች አስከብሮ ወደፊት ለመራመድ በግንቦት የዴሞክራሲ፣ የፍትኅ፣ የሕዝብ ወንድማማችነትና የአገር አንድነት እሴቶች ዙሪያ ሁሉም በአንድ አቅጣጫ የሚገፋበት የሚሊዮኖች ትግል ያስፈልጋል የሚለው እምነት መሆን ይኖርበታል፡፡ በኛ ግምት ዛሬ ኅብረተሰባችን ለሚገኝበት አስከፊ ሁኔታና ለትግሉ አደገኛ መዝረክረክ መሠረታዊ ምክንያት የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ሆን ብለው እኛ ደግሞ በእይታ ጉድለትም ይሁን በሌሎች ምክንያቶች ግንቦት ላይ የትግሉም የድሉም ዋና ባለቤት የነበረው ሕዝባችን ከፖለቲካው መድረክ እንዲገለል ማድረጋችን ይመስለናል፡፡ ዛሬ ከምንገኝበት አጣብቂኝ ለመውጣት ከፈለግን የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችን በአሥራ-አራት ዓመታት የግፍ አገዛዛቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ተከላካይነት ኅብረተሰባችንን ደግሞ ወደማያወላዳ የፖለቲካ የበላይነት ያሸጋገረውን ይኽንን ሕዝባዊ ተሳትፎ መልሶ እውን ማድረግና ሕዝባችን መልሶ የትግሉ ባለቤት መሆኑን ማረጋገጥ የትግላችን ትልም (የስትራቴጂያችን) የማዕዘን ድንጋይ አድርገን መንቀሳቀስ ይኖርብናል፡፡

ዋናው የትግላችን ዓላማ ግንቦት ላይ እኛን ባኮራ፣ ዓለምን ባስደነቀ፣ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎችን ብርክ ባስያዘ ወኔ ሕዝባችን እንደ አንድ ሰው ተንቀሳቅሶ ዴሞክራሲ በአፋኝ አገዛዝ ላይ፣ የሰላማዊ ለውጥ አሳብ በአመፅ ፖለቲካ ላይ፣ የሕዝብ ወንድማማችነትና የአገር አንድነት እሴት በአናክሰህ-ግዛ ርኩስ ፖለቲካ ላይ ድልን ለማጎናፀፍ ያስቻለውን ሕዝባዊ የትግል ማዕበል መልሶ በመቀስቀስ የበጎ አዙሪት ሂደት የመክፈት ዓላማ ነው፡፡ ሆኖም ትኩረታችን በግንቦት እሴቶች ዙሪያ የግንቦት ኃይሎችን በሙሉ አንቀሳቅሰን እንዴት ያኔ የተጎናፀፍነውን የማያጠራጥር የፖለቲካ የበላይነት መልሰን እንያዝ? የሚለው ጥያቄ ላይ መሆን ሲገባው ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ ለምን እንታገል? በሚለው ጥያቄ ላይ ሳይሆን እንዴት እንታገል? በሚለው ነጥብ ላይ ልዩነቶች ሲከሰቱ እናያለን፡፡ ለኛ በመካሄድ ላይ ያለው ክርክር "ሰላማዊ ትግል ወይስ የትጥቅ ትግል" በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የታጠረ ቁንፅል ክርክር ይመስለናል፡፡

በዚኽ በትግል ስልት ጉዳይ አንድ በጣም ግልፅ መሆን ያለበት ቁም-ነገር አለ፡፡ ዛሬ በአገራችን ዓላማውን ለማራመድ ከአመፅ፣ ከሽብርና ከሕገ-ወጥነት ሌላ ምንም ምርጫ የሌለው አንድ ኃይል ቢኖር ሕወሓት/ኢሕአዴግ ብቻ ነው፡፡ የዚያኑ ያኽል ደግሞ ሕዝባዊ የግንቦት ኃይሎች በግንቦት እሴቶች ዙሪያ በአንድ አቅጣጫ ለመንቀሳቀስ እስከተስማሙና የሕዝባችንን የትግሉ ማዕከልነት እስከተቀበሉ ድረስ የትግል ስልት ምርጫው ምንም ወሰን የሌለው፣ ትግላቸውም በምንም ቀኖናዊነት የማይታጠር ዘርፈ-ብዙና ሁሉን አቅጣጫ ያየና የዳሰሰ እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡ በሕዝባችን የትግሉ ማዕከልነት ላይ ስምምነት ካለና ለዚኽና ወደዚኽ ከተሠራ ማንም ይሁን ማን ያመቸኛል በሚለው ስልት ቢሰማራ ይኽ የልዩነትና የክፍፍል ምንጭ መሆን አይኖርበትም፡፡ የሕዝባችንን አጀንዳ እስካነገበ ድረስ ማንም ኃይል "አምንበታለሁ፣ ይቻላል" በሚለው ሕጋዊ ሆነ ሕገ-ወጥ፣ ይፋ ሆነ ኅቡእ፣ ሰላማዊ ሆነ የትጥቅ ትግል መስከ ሊሰማራ የማይችልበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡

ቀስ በቀስ በግንቦት እሴቶች ዙሪያ ሕዝባዊ የትግል ማዕበል የመፍጠር ዓላማ የሌለው እስከሆነ ድረስ "ሰላማዊ" የሚባለው ትግል የጥቂት ግንባር-ቀደም ኃይሎች ግርግር ከመሆን አልፎ የምንፈልገውን የነፃነት ፈር አያስይዘንም፡፡ የግንቦት ኃይሎች የግንቦትን እሴቶች አንግበውና ሕዝባችን የማያጠራጥር የፖለቲካ የበላይነትን መልሶ ጨብጦ ከዳር-እስከ-ዳር በማይንቀሳቀስበት ሁኔታ የተለያዩ ኃይሎች አንዳንዴም የግንቦትን እሴቶች በሚቃረኑ የተሰበጣጠሩ ወገናዊ አጀንዳዎች እናካሂዳለን የሚሏቸው የትጥቅ ትግሎችም የጋራችን ከሆነችው አገርና ከሕዝባችን ዘለቄታዊ ጥቅሞች አንፃር ሲታይ የትም የሚያደርሱ አይደሉም፡፡ ይኽ ማለት ዛሬ አገራችንን በመቆጣጠር ላይ ካሉት ጦር-ጠማሽ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች አንፃር ትጥቅ አንስቶ መፋለም አያስፈልግም ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ሆኖም ከወሳኙ ሕዝባዊ የአንድነትና የጋራ ተጋድሎ አንፃር እነዚኽ ኃይሎች በግንቦት እሴቶች ዙሪያ ሕዝባችን በሚሊዮን እየተቆጠረ ለሚያካሂደው ትግል አጋዥ ሆነው ራሳቸውንም

የዚኽ ታሪካዊ ተጋድሎ“የታጠቀ ክንፍ” አድርገው ካልተንቀሳቀሱና አልፈው ተርፈው ደግሞ ይኽንን ሕዝባዊ ትግል “እንተካለን” ብለው የሚግደረደሩ ከሆነ የትም እንደማይደርሱ በጣም ግልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡

ነገሩ እንደዚኽ ሆኖ ሳለ ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ በአንድ በኩል “ለሰላማዊና ሕጋዊ ትግል” ቆመናል በሚሉና በሌላ በኩል “ያለ ትጥቅ ትግል ስርየት የለም” በሚሉ ወገኖቻችን መኻከል የሚንፀባረቀው ልዩነት ዋናውንና ወሳኙን ሕዝባዊ ተጋድሎ ወደ ጎን ትቶ የሚካሄድ ክርክር ነው ብለን እናምናለን፡፡ <u>የኅብረታችን ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ ኅብረቱ “ሕዝባዊ ሰላማዊ” የትግል ስልት የመከተል ዓላማ እንዳለው የገለፀው እየተካሄደ ባለው ክርክር “የተረሳውን” ሕዝባዊ ተሳትፎና የሕዝባችን የትግሉ ባለቤትነት ጉዳይ መልሶ የትግላችን ትልም (የስትራቴጂያችን) ማዕከል ለማድረግ ካለው ፅኑ እምነትና አቋም በመነሳት ነው፡፡</u> በኛ እምነት ሰላማዊና ሕዝባዊ የሚሉት ቅጽሎች በምንም ዓይነት ተነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም፡፡ ሰላማዊ ትግል ሕዝብን ካልያዘ በአየር ላይ የሚንሳፈፍ ለሕወሓት/ኢሕአዴግ “ዕድሜ-ቀጣይ” ስልት ከመሆን አያልፍም፡፡ ሕዝብ ከዳር-እስከ-ዳር እንደ አንድ ሰው ሆኖ ለአንድ የጋራ ሕዝባዊና አገራዊ ዓላማ በማይንቀሳቀስበት ሁኔታ ደግሞ ዛሬ አገራችን በምትገኝበት ውስጣዊ፣ የአካባቢና ዓለም-አቀፍ የተወሳሰበ ሁኔታ ለሕዝባችን የጋራ ተጋድሎ በአጋዥነት ያልተሰለፈ የትጥቅ ትግል ብቻውን የተወሳሰበን ሁኔታ ይበልጥ ያወሳስባል እንጂ ለጋራ ጥቅም የሚሆን መፍትሔ የሚያመጣ አይሆንም፡፡

ኢዴኃኅ (ኅብረታችን) ከዚኽ ትንተና ተነስቶ ዛሬ የአገራችን አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ሊጠቀሙባቸው ከሚችሉት ከአሸዋ የበዙ ልዩነቶች አንፃር በምንም ቀኖናዊነት ሳይታጠሩ ሕዝብን አንቀሳቅሶ በቁርጠኝነት ታግሎ የማታገል የትግል ትልም (ስትራቴጂ) ለመንደፉ ጉዳይ ቅድሚያ ሰጥተው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል እንላለን፡፡ እንዲህ ዓይነቱ የትግል ትልም (ስትራቴጂ) እጅግ አስቸጋሪና ውስብስብ እንደሆነ፣ ከፍተኛ መስዋዕትነትም እንደሚጠይቅ ግልፅ ነው፡፡ እውን እንዲሆን ከፈለግን ደግሞ አንደኛ ሕዝባችንን በምን በምን አጀንዳዎች ዙሪያ “ተነስ” እንበለው? ሁለተኛ ደግሞ በዚኽ መልክ የምንቀሰቅሰው ሕዝባዊ ትግል እስከ ድል ድረስ ቀጣይነት እንዲኖረው ምን ምን መሠራት አለበት? የሚሉትን ሁለት ጥያቄዎች በበቂና በግልፅ መመለስ ያስፈልጋል፡፡

ለሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል ሕዝባችንን በምን የመታገያ መስመር ዙሪያ (አጀንዳ) እናንቀሳቅሰው? በአሥርተ-ሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ለእስራት፣ ለግድያ፣ ለስደት፣ ለእንግልትና ይኽ ነው ለማይባል መጠነ-ሰፊ ወከባ የዳረገው አምባ-ገነንና ሽብርተኛ አገዛዝ በመፈጸም ላይ ያለው ግፍ ምን ያኽል ዘግናኝ ቢሆንና ምን ያኽል ክቡር የሆነ መስዋዕትነት እየተከፈለበት ቢሆንም የግንቦትን ቅልበሳ መዘዞች በዚኽ በፖለቲካ ገጽታው ወስኖ ማየት ትልቅ ስህተት ይሆናል፡፡ የግንቦት ቅልበሳ ሌላው ዋናው ገጽታና መዘዝ ከሕዝብ ድምፅ ዝርፊያው በተጓዳኝ በኤኮኖሚና በማኅበራዊ መስኮች የተደረገውን “የሕዝባዊ አማራጭ ዝርፊያ” የሚመለከት ነው፡፡ ኅብረታችንም ሆነ ቅንጅቱ በምርጫው ዘመቻ ወቅት የኢሕአዴግን የኤኮኖሚና የማኅበራዊ ፖሊሲዎች በአገር አውዳሚነት ፈርጀው፣ ከኢሕአዴግ መሪዎች ጋር በሕዝብ ፊት ተከራክረው ለሕዝባችንና ለአገራችን ይበጃሉ ባሏቸው በጎ አማራጭ መርኀ-እቅዶች (ፖሊሲዎች) ዙሪያ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ሕዝባችንም የተሻለ ቀን ያመጡልኛል ብሎ በማመን ለነዚኽ አማራጮች ድምፁን ሰጥቷል፡፡ የኢሕአዴግ መሪዎች በሸፍጥ አሸነፍን ሲሉ በሽብር ሊያንበረክኩት በሚፈልጉት ኅብረተሰብ ላይ ምንም ዓይነት ተጠያቂነት በሌለበት ሁኔታ በእነዚህ አጥፊ ፖሊሲዎቻቸው እንቀጥላለን ማለታቸው እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ በዚኽም የተነሳ ዛሬ በግልፅ እንደሚታየው በደርዘን ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በየቀኑ በጣም እየከፋ ለሚሄድ የጠናበት የችግር ናዳ እየተዳረጉ ናቸው፡፡ ቅልበሳውን በወጉ ለመቋቋምና ወደፊት ለመራመድ የሚቻለው ይኽንን **የቅልበሳ ድርብ ገጽታ ተገንዝበን በፖለቲካው መስክ ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊና በኤኮኖሚያዊ ጥያቄዎችም ዙሪያ ሕዝባችንን ይዘን ስንንቀሳቀስ ብቻ ነው፡፡ ይኽ ካልተደረገ ሽብር እና የአመራር ክፍተት ተጋግዘው ግራ ባጋቡት ኅብረተሰብ ውስጥ እነዚኽ ቀውሶች እየተባባሱ ቀጥለው**

በበርካታ የአፍሪቃ አገሮች እንደሚታየው በግልፅ አማራጭ ዙሪያ ሳይሆን ጎልውናዋን ሳይቀር ጥያቄ ውስጥ ሊያስገቡ ለሚችሉ እጅ እግር ለሌላቸው ትርምሶች ልትዳረግ የምትችልበት አደጋ እንዳለ ግልፅ መሆን አለበት፡፡

እስካሁን በዚኽ መልክ የአገራችንን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ዘርፈ-ብዙ በሆነ መልኩ ሳይሆን ግንጥል በሆነ በፖለቲካ መስክ ያተኮረ እንደነበረ ግልፅ ነው፡፡ በቅድመ-ግንቦቱ ወቅት የነበረውን የትግል ልምዳችንን ብንመለከት የምናየው ይኸንን ነው፡፡ በነዚኽ ዓመታት የሕዝባችንን ጉረሮ አንቀው የያዙትን የሰማይ ስባሪ የሚያክሉ የጎልውና ቀውሶች ወደ ጎን ትተን የዳኝነት ነፃነት፣ የሕግ የበላይነት፣ ነፃ ፕረስ፣ የመደራጀት መብት፣ የተቋማት ግንባታ፣ ወዘተ.... እያልን በነዚኽ ክቡር እሴቶች ዙሪያ ከፍተኛ መስዋዕትነትን የጠየቀ ትግል ስናካሂድ ቆይተናል፡፡ የዚያኑ ያኽል ደግሞ ትግሉ እነዚኽን ሁሉ 'እኔም አምንባቸዋለሁ' ብቻ ሳይሆን 'በተግባርም እያዋልኳቸው ነው' እያለ ከሚመፃደቅ የጥፋት ኃይል ጋር ስለ ነበረ ይኸ ሁሉ ምንም የፖለቲካ የበላይነት ያላጎናጸፈን የአህያ ውድቂያ ትግል ሆኖ እንደቆየ ግልፅ ነው፡፡ ከቅልበሳውና ከተከፈለው መስዋዕትነት ባሻገር የግንቦት ድልና ታሪካዊነት ቀጣዩ ትግል እንዳለፈው በፖለቲካው መስክ ከመታጠር አልፎ ሊሄድ የሚችልበት ሁኔታ ማመቻቸቱ ላይ ነው ብለን እናምናለን፡፡

በፖለቲካው መስክ ማን በሃቅ ማን ደግሞ በልፈፋ ደረጃ ለዴሞክራሲያዊ እሴቶች እንደቆመ ለሕዝባችንም ለዓለም-አቀፍ ኅብረተሰብም በግልፅ አሳይቶ፣ የሕወሓት/ኢሕአዴግን መሪዎች እርቃን ያስቀረ ለአገራችን ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የማያጠራጥር የፖለቲካ የበላይነት ያስጨበጠ ሂደት ነበር፡፡ ሁለተኛ ሕዝባችንን በማዋከብ ላይ ያሉት በርካታ የጎልውና ችግሮች ከጅምላ ሥራ-አጥነት እስከ መናጢ ድህነት፣ ከትውልድ-ገዳዩ የትምሕርት ፖሊሲ እስከ ኤች አይ ቪ ኤድስ፣ ረሃብ-ፈልፋይ ከሆነው ፀረ-ገበሬ ፖሊሲ ነጋዴው በሃቅ ነግዶ፣ መዋዕለ-ጥሪት አፍሳሹ (ኢንቬስተሩ) በተረጋጋ ሁኔታ ገንዘቡን አውጥቶ ለራሱም ለአገሩም እንዳይሠራ እጅ ከወርች አስሮ እስከያዘው አድልያኦዊና የጠናበት ሙሰኛ አሠራር፣ በአጭሩ በአገር ኪሣራ ጥቂቶች ለጥቂቶች መበልፀግ የተከተሉትን ሂደትና የደነገጉትን ኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሥርዓት በማጋለጥ ሰፊ ዘመቻ ተካሂዷል፡፡ ዛሬ በዚኽ እምርታ ቀጥለን የቅልበሳውን መዘዞች በሙሉ ፊት ለፊት ከመግጠም ይልቅ ይኸንን ድርብ ግኝት የትም በትነን እንደ ቅድመ-ግንቦቱ ዘመን ዛሬም ተመልሰን በፖለቲካው ግንጥል ትግል ጎዳና እየተሰማራን እንገኛለን፡፡ የተያዘው የሰዶ-ማሳደድ የትግል ትልም (ስትራቴጂ) እነዚኽን ሚሊዮኖች እየተቀጡባቸው ያሉ ከባድ ቀውሶች ከገፈት ቀማሹ ሕዝብ ጋር አብሮ የመዋጋት የትግል ሂደት ሳይሆን ግፉንና መከራውን "ለቀባሪ ለማርዳት" በሚግደረደሩ መግለጫዎች "በማጋለጥ" የተወሰነ አካሄድ ነው፡፡ ይኸንን "ፍየል ወዲህ ቅምዝምዝ ወዲያ" የሚመስል አጉል አካሄድ እየያዝን ያለነው በኅብረተሰባችን ላይ በመውረድ ባለው አፈናና ሽብር በመዋከባችን ላይ በመሆናችን ብቻ አይደለም፡፡ ከዚኽ ይልቅ መሠረታዊ የሆነ የእይታ ችግር ያለብን ይመስለናል፡፡

የመጀመሪያ ችግር የሕዝባችንን ተጨባጭና የጎልውና ጥያቄዎች "በይደር" ለማስቀመጥ የሚታየው አባዜ ነው፡፡ ለዚኽም የሚቀርበው ክርክር ደግሞ ተደጋግሞ ተሰምቷል፡፡ እናውቀዋለን፡፡ ይኸውም "ዛሬ ዋናው ተግባር ለዴሞክራሲና ለዴሞክራሲ ተቋማት የሚደረገውን ትግል ማፋፋም ነው፡፡ ከዚያ ዴሞክራሲ ሰፍኖ ነፃ ምርጫ ሲደረግ ሁሉም አማራጭ ፕሮግራሙን ይዞ ሕዝብ ፊት መቅረብ" ይችላል የሚል ክርክር ነው፡፡ ከዴሞክራሲው ትግል ድል ባሻገር ይደረስባቸዋል በሚል ስሌት በግንቦት የምርጫ ዘመቻ ወቅት አንግበን የተንቀሳቀስንባቸው አማራጭ ሰነዶች፣ የእኛ ትግል እናቱም አባቱም የምርጫ ሰሞን ግርግር ይመስል፣ ገና ዘንቦ ተባርቆ የሚደረግ ነፃ ምርጫ ሲመጣ በሚል ጨርሶ ተረስተው "የክት ቀን" ሰነዶች ሆነዋል፡፡

ከዚኽ ተያይዞ እንዲህ ዓይነቱን አጓጉል አካሄድ ለመደገፍ የሚቀርብ ሌላም ክርክር አለ፡፡ ይኸውም ያለንበት ሥርዓት መሠረታዊና የዝቅተኛም ዝቅተኛ የሚባሉ መብቶችን

እንኳን ረግጦ የያዘ በመሆኑ “ሥራ ለሥራ-አጡ፣ ምግብ ለተራበው፣ መናጢ ድህነት በቃን፣ የአካባቢ ውድመትና የአየር ብክላ ምድራችንን እያጠፋ ነው፣ ወዘተ...” እየተባለ የሚካሄድ ትግል ጨርሶ “የሚፈቅድ” ስላይደለ መጀመሪያ እንዲህ ዓይነት ትግል “ለሚቻልበት” ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንታገል የሚል አስገራሚ ክርክር ነው:: እርግጥ ያለንበት ሥርዓት ሕዝብን ይዞ የሚነሳ ማንኛውንም ጥያቄ ከለየለትና በአመፅ መደምሰስ ካለበት “የነውጠኞች ሴራ”፣ ማንኛውንም ሕዝብን ይዞ የሚካሄድ ሰላማዊና ሕጋዊ ተጋድሎ “ሕገ-መንግሥታዊውን ሥርዓት በአመፅ ለማፍረስ” ከሚደረግ እንቅስቃሴ፣ ወዘተ... ለይቶ ማየት የማይችል እጅግ ኋላ-ቀር የሆነ ሥርዓት ነው:: ከዚኽ እውነታ ተነስተን ግን **ለአለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ የሚመጥን የትግል ትልም (ስትራቴጂ) ነድፈን እንንቀሳቀስ እንላለን እንጂ** “ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዳንታገል ፀረ-ዴሞክራሲያዊው ሥርዓት አስቸገረን ወይም አይፈቅድም” ብለን ማቆም አንችልም:: ዞሮ ዞሮ ደግሞ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ፈቀዱት አልፈቀዱት በሕዝብ ብሶቶችና ጭንቀቶች ዙሪያና ለሕዝብና ለአገር ዘለቄታዊነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ሕዝብን ይዘን እስካልታገልን ድረስ በነ ራእይ ብቻ አንግቦ በሚካሄድ ትግል እነዚኽን የሕዝብ ጥያቄዎች ለማስተናገድ የሚያስችለን “ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት” እናመጣለን ማለት አደገኛ የሆነ የህልም ዓለም ውስጥ መኖር ይሆናል::

ኢዴኃኅ ሕዝባዊ-ሰላማዊ ትግል ሲል:-
አንደኛ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ብሶታቸውን አንግበው ለችግራቸው መፍትኄ ለመሻት እንዲታገሉ መቀስቀስና ማደራጀት ያስፈልጋል ማለቱ ነው::
ሁለተኛ እነዚኽ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተራ በተራ መነሳታቸው ተራ በተራ ከመመታት የማያልፍ አጉል መስዋዕትነት እንዳይሆን ሁሉም “ብሶትህ ብሶቴ” በሚል መንፈስ በትግግዝና በአንድነት እንዲነሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል ማለቱ ነው::
ሦስተኛ በዚኽ መልክ የሚንቀሳቀሱት የኅብረተሰብ ክፍሎች ዛሬ የሚገኙበት ከባድ ቀውስ የግንቦት ቅልበሳ መዘዝ እንደሆነ እንዲገነዘቡና ማንኛውም ዘላቂነት ያለው መፍትኄ ከሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ከሥልጣን መወገድና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ በሕዝብ ፊት ተጠያቂ የሆነ መንግሥት መመሥረት እንደሆነ አውቀው እዚያው በዚያው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲታገሉ መቀስቀስ ያስፈልጋል ማለቱ ነው::
ይኽንን ተግባር ለመፈጸም እንዲቻል ደግሞ የአገራችን አገር-ወዳድና ዴሞክራቶች ሁለት ነገሮችን ማሟላት ይኖርባቸዋል::

አንደኛ ሕዝባችንን ለእንደዚኽ ዓይነቱ ዘርፈ-ብዙ ተጋድሎ “ተነስ” ብለን ተደማጭነት ለማግኘት ከፈለግን ከሁሉ በፊትና በቅድሚያ ተቃዋሚዎች ግንቦት ላይ የነበራቸውንና ዛሬ በተደጋጋሚ በተፈጸሙ ስህተቶች ምክንያት የትም የበተኑትን **ተአማኒነት መልሰው ማግኘት ይኖርባቸዋል::** ሕዝባችን አንዴ ሰልፍ ውጣ ተብሎ ወዲያው ደግሞ ያ ሰልፍ ተሰርዟል ሲባል፣ አንዴ ቀትር ላይ ቤት ለመዋል አድማ ተሰናዳ ተብሎ ለዚኽ ጥሪ ተግባራዊነት ሲሰናዳ ማምሻው ላይ መሪ ተብየዎቹ ከባዕዳንና ከአቶ መለስ ጋር ተመሳጥረው አድማው ተሰርዟል ብለው ሲያረዱት፣ አንዴ አገራዊ ጉባዔ ተብሎ ከሰባት መቶ በላይ የሚሆኑ ታጋይ ዜጎች ከአገሪቱ አራቱም ማዕዘናት አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ “አዳራሽ ጠፋ” በሚል ተልካሻ ሰበብ ጉባዔው ተሰርዞ ሁሉም አንገቱን ደፍቶ ወደ መጣበት እንዲመለስና የኢሕአዴግ ጨካኝ ካድሬዎች ጥርስ ውስጥ እንዲገባ ሲደረግ የታዘበ ሕዝብ ነው:: እንዲህ ዓይነቱ የመመሪያዎች ዥዋዥዌ ታጋዩን ሕዝብ ግራ እንዳጋባና በመሪዎቹም ላይ የነበረው አመኔታ እንዲሟሽሽ እንዳደረገው ግልፅ ነው:: ይኽ አልበቃ ብሎ ትላንት የድርጅት አጥር ሳያግዳቸው እጅ ለእጅ ተታይዘው ለትግሉ አመራር ይሰጡ የነበሩ ኃይሎች ዛሬ በትንሹም በትልቁም ዞሮ ዞሮ ከሕዝባችንንና ከአገራችን ችግሮች አንፃር እዚህ ግቡ ሊባሉ በማይችሉ ልዩነቶች ሲከፋፈሉ ማየቱ መሪዎች የነበራቸውን ተአማኒነት ገደል እንዳስገቡት ገሃድ ነው:: ይኽንን አለመረዳት እራስን ማታለል ብቻ ይሆናል:: ከዚኽ ይልቅ የሕዝባችንን ትግል እንመራለን የሚሉ ኃይሎች ይኽንን ሃቅ ተገንዝበው በአንድ በኩል መከፋፈልንና መቦጫጨቅን ትተው **“በአንድነት ተነስ” በሚሉት ሕዝብ ፊት እራሳቸው አንድ ሆነው**

በመቆም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጥራት ብቻ ሳይሆን ፅናት ያለው አመራር ለመስጠት በመሞከር የፈራረሰውን ተአማኒነት <u>መልሶ መገንባት</u> ይኖርባቸዋል።

ይኸንን ሕዝባዊ ትግል ለመምራት በዚኸ መልክ ግንቦት ላይ የነበረውን ተአማኒነት መልሶ መገንባት ብቻ አይበቃም። <u>የአመራር ቀጣይነትም</u> ሊታሰብበበት የሚገባው ቁልፍ ጥያቄ ነው እንላለን። ግንቦት ላይ እነ አቶ መለስ ዜናዊ "እንከን የለሽ" ምርጫ እናካሂዳለን ብለው በመለፈፋቸው፣ ሕዝባችን እየተንገላታም፣ እየተዋከበም እየተሰዋም ቢሆን በሰላም ለምድር አንቀጥቅጥ ሰላማዊ ሰልፎች መውጣት መቻሉ፣ ሕዝባዊ ስብሰባዎች ከሞላ ጎደል በቀነሰ ችግር መካሄዳቸው፣ ፕረሱ ከሞላ ጎደል የሕዝብ ልሳንነቱን አረጋግጦ መንቀሳቀስ መቻሉ፣ ተቃዋሚዎች "ከመንግሥት እኩል ቤት ገብተው" በሕዝብ ፊት መከራከር መቻላቸው፣ ወዘተ.... ይኸ ሁሉ ለትግላችን ከወዲሁ ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሥርዓት ውስጥ የሚካሄድ "ሥልጡን" ገጽታ ሰጥቶ አጉል መዘናጋትን እንደፈጠረ ዛሬ ግልፅ ይመስለናል። በዚኸ መዘናጋት የተነሳ ከግንባር-ቀደሙ ኃይል የተወሰነው ክፍል "ችግር ቢመጣስ?" በሚል የጥንቃቄ አካሄድ ይፋ ከመውጣት ተቆጥቦ ፀረ-ሕዝቡ ክፍል ሊደርስበት የማይቻለው ጠንካራ የሆነ ተደራራቢ መዋቅር እንዲገነባ ጥረት አልተደረገም። በዚኸም የተነሳ መሪዎቹ ከያሉበት ተለቅመው ሲታፈሱ ሕዝባችን፣ በተለይ ደግሞ ወጣቱ፣ የረባ መሪና ሁነኛ አስተባባሪ፣ አስተማማኝ መዋቅርና ኃይል አጥቶ ትግሉን በደመ-ነፍስ፣ በግብታዊነትና በተበታተነ ሁኔታ ለማካሄድ ተገድዶ የከፈለውን ከባድ መስዋዕትነት ሁላችንም እናውቀዋለን። ዛሬ ቀጣይነት ያለው አመራር ስንል ከዚኸ ሕዝባችን አይከፍሉ መስዋዕትነትን እንዲገብር ካደረገው ስህተት በቂ ትምሕርት ቀስመንና ተምረን፣ ሰላማዊና ሕዝባዊ ትግላችን የሚያስፈልገውን <u>ቀጣይነት ያለው አመራር</u> እውን ለማድረግ ያለው ሁኔታ በሚጠይቀው መጠን በጥንቃቄ የሚገነባ ተደራራቢ አወቃቀር እንዲኖርና ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ የግድ ይሆናል ማለት ነው።

<u>ይኸን ተአማኒነት መልሶ የመገንባቱና የትግሉን አመራር ቀጣይነት የማረጋገጡ ተግባር ዛሬ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ የዴሞክራሲና የአንድነት ኃይሎች በሙሉ የጋራ ተልዕኮ መሆን ይኖርበታል።</u> ኅብረታችን ካለፉት ድሎችም ሆኑ ድክመቶችና ውድቀቶች ትምሕርት በመቅሰም ብቻ ሳይሆን ካለንበትም ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ለዚኸ የጋራ ተልዕኮ መሳካት በበኩሉ የሚያደርገውን አስተዋጽዖ ለማጎልበት አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን የአወቃቀርና የአሠራር ለውጦች አድርጓል። ሆኖም በግንቦት እሴቶች ዙሪያ ሕዝባችንን አንቀሳቅሶ የቅልበሳውን መዘዞች እየተቋቋሙ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር የሚደረገው ትግል የግንቦት አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ታሪካዊ ተልዕኮ መሆኑን አሁንም በአፅንዖት ለማስረገጥ ይወዳል። ከዚኸም በመነሳት ለቀጣዩ ዘርፈ-ብዙና ውስብስብ ትግል የዚች አገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ኃይሎች በጋራ መክረውና ዘክረው የጋራ የትግል ትልም (ስትራቴጂ) ለመንደፍና ታግሎ የሚያታግል የጋራ የሆነ መድረክ ለመፍጠር እንዲችሉ ከዚኸ በፊት በተደጋጋሚ ባደረግነው ጥሪ መሠረት አንድ አገር-አቀፍ የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ለመምከር ፈቃደኛ ከሆኑ ወገኖች ጋር የምክክርና የዝግጅት የጋራ አካል *(Steering Committee)* በአስቸኳይ ለመፍጠር ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ዝግጁ መሆኑን ለማብሰር ይፈልጋል።

ድል በኅብረት፣ ኅብረት ለድል!
የተባበረ የሕዝብ ትግል ምን ጊዜም አቸናፊ ነው!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

ሐምሌ ፪ ሽህ ዓ/ም